FGM/C የሴት ብልት ውጫዊ አካል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መወገድን ወይም በሴት ብልት የአካል ክፍሎች ላይ የሚደርስ ሌላ ጉዳት/ ከህክምና ውጭ የሆኑ ሂደቶችን ሁሉ ይገልጻል። በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች “የሴት ግርዛት” ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ልምምዱ ምንም አይነት የጤና ጠቀሜታ የሌለው ሲሆን ለአጭር ጊዜ እና ለረጅም ጊዜ የአካል እና የአእምሮ ጤና ችግሮች ያስከትላል።

## FGM/C የሚያስከትላቸው የጤና ተጽእኖዎች ምንድን ናቸው?

ወዲያውኑ የሚያጋጥሙ ተጨማሪ ህመሞች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- ከባድ ህመም
- ከመጠን ያለፈ ደም መፍሰስ (መድማት)
- የመራቢያ አካል ህብረህዋስ እብጠት
- ትኩሳት
- ኢንፌክሽኖች፣ ለምሳሌ: ቴታነስ
- የሽንት መሽናት ችግሮች
- የቁስል አለመዳን ችግሮች
- የብልት ዙሪያ ህብረህዋሳት ጉዳት
- ድንጋጤ
- ሞት

የረጅም ጊዜ ተጨማሪ ህመሞች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ:

- የሽንት መሽናት ችግሮች (በመሽናት ወቅት የሚፈጠር ህመም፣ የሽንት ቱቦ ኢንፌክሽን)
- የሴትብልት ችግሮች (ፈሳሽ፣ማሳከክ, የባክቴሪያ ቫጂኖሲስ እና ሌሎች ኢንፌክሽኖች)
- የወር አበባ ችግሮች (በወር አበባ ወቅት መሰቃየት፣ የወር አበባ ደም አለመውጣት ችግር፣ ወዘተ)
- የቲሹ ጠባሳ እና ኬሎይድ
- የግብረ ስጋ ግንኙነት ችግሮች (በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት መታመም፣ የእርካታ መቀነስ፣ ወዘተ)
- በወሊድ ወቅት የሚያጋጥሙ ተጨማሪ ህመሞች ከፍተኛ ስጋት (በወሊድ ወቅት መቸገር፣ ከመጠን ያለፈ ደም መፍሰስ፣ በቀዶ ህክምና ለመውለድ መገደድ፣ ህጻኑን ማንቃት3 አስፈላጊ መሆን፣ ወዘተ) እና የተወላጅ ህጻናት ሞት
- ቆይቶ ለቀዶ ህክምናዎች መገደድ
- የሥነ ልቡና ችግሮች (ጭንቀት፣ መሰላቸት፣ የድህረ ክስተት ጭንቀት ችግር፣ ለራስ የሚሰጥ ክብር ዝቅ ማለት፣ ወዘተ)

**ስለ FGM/C የጤና ተጽእኖዎች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የአለም የጤና ድርጅት ድህረገጽን በ https://www.who.int/news-room/fact-sheets/detail/femalegenital-mutilation ይጎብኙ።**

## በሚከተሉት ሁኔታዎች መረጃ ወይም ድጋፍ ለማግኘት ለChildhelp National የህጻናት ጥቃት ሆትላይን በስልክ ቁጥር 800-4-A-CHILD (800-422-4453) ይደውሉ:

- በከፍተኛ የFGM/C ስጋት ላይ እንደሆኑ ካመኑ;
- FGM/C ከተፈጸመብዎ;
- ሥለ FGM/C በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎ;
- ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ FGM/C ስለሚፈጽም ሰው የተመለከተ መረጃ ካሉዎ፣ ወይም
- በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም በሌላ አገር የሚገኝ የFGM/C ስጋት ያለበትን ሰው የሚያውቁ ከሆነ።

**FGM/C ከተፈጸመብዎ ወይም በFGM/C ስጋት ውስጥ ከሆኑ ለተወሰኑ ለወንጀል ወይም ስደት ተጎጂዎች ለሚቀርቡ የስደተኛ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት:
**uscis.gov/humanitarian/female-genitalmutilation-or-cutting-fgmcን ይጎብኙ።**

U.S. Citizenship and Immigration Services



# የሴት ብልት ውጫዊ አካል በከፊል ማስወገድ ወይም መቁረጥ

FGM/C

U.S. Citizenship and Immigration Services

M-1169

## FGM/C ከተፈጸመብዎት:

- ጥፋቱ የእርስዎ አይደለም።
- ህደቱ በእርስዎ ላይ ከመፈጸሙ የተነሳ የትኛውንም የዩ.ኤስን ህጎች አልጣሱም።
- ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመጓዝ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ የስደተኛ ጥቅማ ጥቅሞችን በመቀበል ብቁነትዎ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አይኖረውም።

የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከላት የሥነ ተዋልዶ ጤና ምድብ (CDC) ተመራማሪዎች ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቀደም ሲል እስከ

**500,000**

የሚደርሱ ልጃገረዶችና ሴቶች FGM/C እንደተፈጸመባቸው ወይም ወደፊት የFGM/C መፈጸም ስጋት እንዳለባቸው ይገምታሉ።

በአፍሪካ፣ መካከለኛው ምስራቅና እሲያ ውስጥ በሚገኙ FGM በስፋት በሚዘወተርባቸው

በ**30** አገራት ውስጥ የሚገኙ

ከ**200**

ሚሊዮን በላይ ልጃገረዶችና ሴቶች የተገረዙ ናቸው።

እስከ 2030 ዓ.ም ድረስ ልማዱ አሁን በሚገኝባቸው ደረጃዎች የሚቀጥል ከሆነ በየዓመቱ

**4.6** ሚሊዮን ልጃገረዶች ለFGM ስጋት ዉሰጥ ይሆናሉ።

## የዩ.ኤስ መንግስት FGM/Cን ይቃወማል።

የዩኤስ መንግስት ምንም አይነት ዲግሪ፣ ወይም ክብደት፣ እና ምንም አይነት ተነሳሽነት ቢኖረውምየሴት ልጅ ግርዛትን ይቃወማል፣ የዩኤስ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛት በባህላዊ እምነቶች መሰረት እና እንደ የአዋቂነት አጀማመር የአምልኮ ሥርዓቶች ሊፈጸም እንደሚችል የሚገነዘብ ቢሆንም የሴት ልጅ ግርዛትን እንደ ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ፣ እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እና የህጻናት ጥቃት አድርጎ ይመለከተዋል። .

## ዩናይትድ ስቴትስ FGM/C እንዲያበቃ ለማድረግ በትጋት ትሰራለች።

የሴት ልጅ ግርዛት/ FGM/Cን ማስቆም የአሜሪካ መንግስት የሴቶችን እና ልጃገረዶችን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ እና መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚያደርገው ጥረት አካል ነው። የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሴት ልጅ ግርዛት ስለሚያስከትላቸው አደገኛና ጎጂ ውጤቶች ሰዎችን ለማስተማር በዩናይትድ ስቴትስ እና በሌሎች አገሮች እየሰራ ነው።



## ከ18 ዓመት በታች በሆነ ሰው ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈፀም መሞከር ወይም ድርግቱን ለመፈፀም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ማምጣት ወይም ከዝያ ውጭ ለማጓጓዝ መሞከር የዩኤስ ህግ ተቃራኒ ነው። እንዲሁም ወላጆች ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎች ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን መፍቀድ ወይም ማመቻቸት ከዩኤስ ህግ ጋር የሚጋጭ ነው።

የሕግ ጥሰት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት፣ መቀጮ ወይም በሁለቱም ያስቀጣል። በወግ ወይም በባህል ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈጸም የተለየ ነገር የለም። ከ18 ዓመት በታች የሆነች ሴት የሴት ብልት መቁረጥ ወይም ብልትን የሚጎዱ ሌሎች ሂደቶች ማከናወን በአሜሪካ ህግ የተከለከሉ ናቸው። በተጨማሪም፣ በዩናይትድ ስቴትስ ያለ ማንኛውም ሰው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናት ሴት ያለእሷ ፈቃድ የሴት ልጅ ግርዛትን የፈፀመ ማንኛውም ሰው በክልል ህግ በወንጀል ሊከሰስ ይችላል።

## በFGM/C/የ ሴት ልጅ ግርዛት ላይ ህግን መጣስ የኢሚግሬሽን መዘዝ ሊያስከትል ይችላል።

የሴት ልጅ ግርዛት/ FGM/Cን መፈጸም ወይም መርዳት የወንጀል ክስ ባይቀርብበትም እንኳ አጥፊውን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዳይገባ መከልከልን ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ እንዲወጣ ማድረግን እንዲሁም ለአንዳንድ የኢሚግሬሽን ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ እንዳይሆን ማድረግን ጨምሮ ከፍተኛ የኢሚግሬሽን መዘዞችን ሊያስከትል ይችላል።

## እርስዎ:

- በFGM/C ስጋት እንዳሎትካመኑ;
- FGM/C ከተፈጸመብዎ;
- ሥለ FGM/C በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎ;
- ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ FGM/C ስለሚፈጽም ሰው የተመለከተ መረጃ ካሉዎ፣ ወይም
- በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም በሌላ አገር የሚገኝ የFGM/C ስጋት ያለበትን ሰው የሚያውቁ ከሆነ፤

## እባክዎ መረጃ ወይም እገዛ ለማግኘት የሚከተሉትን ያነጋግሩ:

- Childhelp National Child Abuse Hotline: 800-4-A-CHILD (800-422-4453)
- U.S. End FGM/C Network: en  dfgmnetwork.org